### 2.4.3 እስከ የሚለው ፍቺ

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ "እስከ" የሌለው ቃል መጨረሻ የሌለው እስከ (Infiniste until) ነው። ቅዱስ መጽሐፉችን መጨረሻ የሌላቸውን ድርጊቶች በእስከ ያስቀምጣቸዋል። እስከ የሚለው ወቅትን መጠነ ጊዜን(Time interval) አያሳየንም። ምሳሌ ይሆን ዘንድ ሊያስረዱ የሚችሉ ጥቅሶችን ምንመልከት።

- 1ኛ ዘፍ 8፡7 "ውሃው እስከሚጎድል ድረስ ቁራው አልተመለሰም" እንደ እነርሱ አባባል ከሆነ ተመልሷል ያሰኛል ቁራው ግን ውሃውም ከጎደለ በኋላ አልተመለሰም። እስከመጨረሻው ማለት ነው።
- 2ኛ 2ሳሙ 8፡23 "ሜልኮም እስከሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም" ይላል ሰው ከሞተ በኋላ ልጅ እንደማይወልድ እናውቃለን የጊዜ ገደብን ወቅትን የሚያሳይ ቢሆን ከሞተች በኋላ ወለደች ያሰኝ ነበር ነገር ግን እስከ የሚለው ቃል መጨረሻ የሌለው መሆኑን ያመለክታል።
- 3ኛ ማቴ 18፡22 "ኢየሱስ እንዲህ አለው እስከ ሰባ ጊዜ እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም" ጌታችንን ጴጥሮስ ስለይቅርታ ጠይቆት የሰጠው መልስ ነው። እስከ ብዙልና አባዝተን ወይ ደምረን የሆነ ቁጥር ድረስ ይቅር በለው ከዛ በላይ ይቅር አትበል ማለት አይደለም። መበደሉን እውቆ ይቅርታ የሚጠይቀውን ሁሉ እስከ መጨረሻው ይቅር ማለት እንደሚገባ ያሳያል። ነገር ግን እንደ ፕሮቴስታንቶቹ አገላለጽ ከሆነ ወንድምህን ይቅር ማለት ያለብህ እስከ ተወሰነ ቁጥር ነው ያሰኛል ይህ ደግሞ በምህረቱ ባለጠጋ የሆነውን እግዚአብሔርን ማሳዘን ይሆናል።
- 4ኛ ማቴ 28፡19-20 "እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ" አለም ከተፈፀመ በኋላ ከእነርሱ ይለያል ማለት ነውን? አይደለም እስከ ፍፃሜው ከእናንተ ጋር ነኝ ማለቱ ነው።



- 5ኛ ሮሜ 5፡14 "ከአዳም አንስቶ እስከ ሙሴ ሞት ነገሠ" ይህ እንደፕሮቴስታንቶቹ አገላለጽ ከሆነ ከሙሴ በኋላ ሞት አልነገሠም ቀርቶአል ማለት ነው ግን ይህ አይደለም።

እንግዲህ ከላይ ያየናቸው በሙሉ እስከ የሚለው ቃል መጨረሻ የሌለው መሆኑን ነው።

እስከምትወልድ ድረስ አላወቃትም ነበር የሚለው እስከ መጨረሻው በግብር አላወቃትም የሚል ነው። ከዛ በኋላ የሚል ፍቺ የለውም።

⇒ እንድም ሥራው ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ አላወቀም ነበር። ምክንቱም ማቴ 1፡19 ላይ በስውር ሊተዋት አስበ ይሰናል።

⇒ ፍጡራንን ሁሉ የፈጠረ ክርስቶስ ያለ ዘር እንዲወለድ አላወቀም ሮሜ 3፡21

⇒ ከንጹህ ዘር የተገኘች ድንግል የእግዚአብሔር ማደሪያ እንድትሆን አላወቀም ሉቃ 1፡35

እነዚህ ፈቺዎች የያዘ እንጂ ፈጽሞ እነርሱ እንደሚሉት አይደለም። ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የሰው ወገን የሰው ዘር የሆነች የጥንተ አብሶ ኃጢአት ያልደረሰባት ያላገኛት የአምላክ እናት በንቱም ድንግልና ዘላለም ድንግል የሆነች እንደሆነ ሊታወቅ ይገባዋል።

### 2.5 የሁላችን እናት ብጽዕት አመቤት

- መዝ 86፡4 "ሰው እናታችን ጽዮን ይላታል በውስጥዋም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱ ልዑል መሠረታት።"

ይህ ስለ ድንግል ማርያም የተነገረ ትንቢት ነው ጽዮን የተባለችው ድንግል ነች ጽዮን የእግዚአብሔር ታቦት የእግዚአብሔር አድሮባታል በርሱም ሆኖ ያነጋገራቸው ነበረ። ዘፀ 25፡22 ድንግ ወላዲተ አምላክም እግዚአብሔር በርሷ ስላደረ በጽዮን ተመስላለች በውስጥዋ ሰው ተወለደ ይላል። በጽዮን ታቦት ውስጥ የትኛው ሰው ነው የተወለደው ብለን ብንጠይቅ

ስለ ጽዮን ታቦት እንዳልተነገረ እናስተውላለን። ጽዮን በተባለት በድንግል ማኅፀን ግን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶአል። ራሱ ልዑል መሠረታት እንዳለው እርሱ አጽንቶአታልና መሥርቶአታል፣ ፈጥሮአታል፣ አንጽቶአታል፣ ቀድሶአታልና በርሷ ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲወለድ ወደደ። ስለዚህም እኛ ድንግልን ወላዲተ አምላክን እናታችን እንላታለን።

ና

- ዮሐ 19፤26 "ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት ከዚህ በኋላ ደቀመዝሙሩን እናትህ እነኋት አለው።"

ይህ ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ አማካኝነት የእርሱን እናት ለሁላችን እናት አድርጎ የሰጠበት ነው። እንግዲህ እኛ ከጌታ እንበልጣለን? የክርስቶስን እናት እናታችን ማለት ሲገባ ለርሷ ክብር ምስጋና ይግባትና በድፍረት እህታችን የሚሉ አሉ። በጣም ባይታደሉና ባያስተውሉ እንጂ ልጇን አምላካችን ብለን ስንጠራ እናቱን እናታችን ብለን ልንጠራት የተገባን ለዚህ ነው። ቅ/ተዋህዶ ሃይማኖታችንም የቀራኒዮውን ሰው ክርስቶስ አምላካችን የሰጠንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በፈተተች ቁጥር ከእግረ መስቀሉ ሥር የተገኘችው እናታችንን ታስታውሳለች። እርሷ ለሁላችን እናት ነችና።

እነኋት እናትህ እንዳለው ሁሉ እኛንም ልጆች አድርጎናል የቅ/ድንግል ልጆች፣ ለዚህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ በመልዕክቱ እንዲህ ያለው "ትዕዛዝን ከአብ እንደተቀበልን ከልጆችሽ በእውነት የሚሔዱ አንዳንዶችን ስለ አገኘኋቸው እጅግ ደስ ብሎኛል አሁንም እመቤቴ ሆይ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እለምንሻለሁ።" 2ዮሐ 1፤5 እኛም ለርሷ ልጆች አድርጎ እናት የሰጠን አምላካችን ነው።



በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው የተለያዩ እናቶች ልጆቻቸውን ከሞት፣ከጥፋት፣ ከባርነት ከሕመም ከደዌ እንደዳኑ ሁሉ እንዲሁ እናታችን ቅ/ድንግል ማርያም በምልጃዋ እያንዳንዳችንን ከሞት ከጥፋት ከሰይጣን ባርነት ከሕማም ከደዌ በልመናዋ ታድነን ዘንድ ጌታ እናት አድርጎ ስጥቶናልና። እግዚአብሔር የተመሠገነ ይሁን የእርሷን እናትነት ያልተቀበለ እንዴት የጌታን አምላክነት ሊቀበል ይችላል ወደ ማስተማዋል ሕሊናቸውን ይመልስለን። ለሁሉ የሚገባውን መስጠት የተገባ ነውና ሮሜ 13፤7 በእናቶቻቸው ጸሎት የተረፉትን ቀጥሎ ባለው ላይ ተመልከቱ ዘፍ፡ 27፤42,1ኛ ነገ17፤17-24,2ኛ ነገ 4፤1-8, ማቴ 15፤21-28

### 2.5.1 ብፅዕት ናት በዚህ ላይ የሚነሱ ጥቃቄዎች

- ሉቃ 1፤48 "እነሆ ከዛሬ ጀመሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል።" ድንግል ብፅዕት የተመሰገነች እናት ነች። ስለዚህም እኛም የትውልዱ ክፈሎች ነንና ብፅዕት ልንላት ይገባል።
- መዝ 44(45)፤17 "ለልጅ ልጅ ሁሉ ስመሽን ያሳስባሉ" እንደለ ስሟን ብፅዕት እመቤት እያልን ልናሳስብ ይገባናል።

<u>ተጨማሪ በዚህ ላይ የሚነሱ ጥያቄች</u>

☞ ሉቃ 8፤21 "እናቴና ወንድሞቼስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉ እነዚህ ናቸው"

ይህ አገላለጽ እናቱን መንቀፉ ሳይሆን ያን ጊዜ ጌታ በማስተማር ላይ ነው። ስለዚህ ቃል እግዚአብሔርን ማቋረጥ ስለማያስፈልግ ይሆን አለ። ይኸውም አባባሉ እናተና ወንድሞቼ እንደሚፈልጉኝ እንዚህን ቃሌን ለመስማት ይፈልጉኛል። የጌታም ዋና አላማ ወደዚ አለም የመጣው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስተማር ነው። ስለሆነም በፅረፍት

መምግብም ማስተማርን አያቋርጥም ነበር ዮሐ 4፥31 ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው መልስ ከዚህ ጋር አንድ ነው እንጂ በድንግልና ፀንሣ በድንግልና የወለደችውን፣ አዝላ በረሃ ለበረሃ እሾህ እየወጋት፣ እንቅፋት እየመታት፣ ውሃ ጥም ረሃብ እያቃጠላት የተሠደደችውን እናቱን መንቀፉና አላውቅሽም ማለቱ አይደለም። ያውም እሱ ለሰው ልጆች እናትና አባትህን አክብር ዘፀ 20፥12 ብሎ ያዘዘ ነው። ታዲያ ጌታ ለምን እፍራሽ ነውን? እንዲሁም ጌታ በመቅደስ እኔ ከሰማይ የወረድኩ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ እያለ ሲናገር ይህ ሰው ሰምቶ ስለ ነበር ሰማሚማት ፈልጎ ሩንቅ ብእሲ (ተራ ሰው) ነህ ለማለት እነሆ እናትህና ወንድሞችህ ፈልገሃል ቢለው ጌታም በሰውየው ልብ ውስጥ ያለውን ክፋት ተመለክቶ ይህን መልስ ሰጥቶታል።

☞ ሉቃ 11፥27 "ይህን ሲናገር ከሕዝቡ እንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ የተሸከመችህ ማህፀንና የጠባሐቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው። እርሱ ግን አዎን ብፁእንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው"

☞ እዚህ ላይ ልናስተውሰው የሚገባ ሴትየዋ የተናገረችውን ስሕተት ስላልነበር "አዎን" ብሎአታል። ልክ ነሽ የተሸከመችኝ ማኅፀንና የጠባኋቸው •ጡቶች ብፁዓን ናቸው። ደግሞም ብፁዓን ሊሆኑ የሚችሉ አሉ። ትክክል ናትና አዎን ብሏታል። ይህቺ ሴት አቀራረቧ አመስግና ለመመስገን ስለነበር ለውዳሴ ከንቱ ስለነበር አመጣጧን አይቶ መሰሳት እንግዲህ አንቺም ቃሌን ሰምተሽ ብጠብቂው ብፅዕይት ትሆኛለሽ ሊላት ወዶ እንጂ አንዳች ተቃውሞ አናገኝበትም።



# ምዕራፍ ሦስት

# ቅዱሳን መላዕክት

## 3.1 የቅዱሳን መላዕክት ተፈጥሮ

ቅድሳን መላዕክት እግዚአብሔር በዕለተ እሁድ ከፈጠራቸው ፍጥረታት አንዱ ፍጥረት ናቸው ኩፋ 2፥6-8 የመላዕክት ተፈጥሮ ከእሳትና ከንፋስ እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል። 3 መቃ. 2፥10-11 መላዕክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሣት ነበልባል መዝ 103፥4

መላዕክት በአንድ ጊዜ የተፈጠሩና በየጊዜው የማይባዙ ናቸው። መላዕክት በተፈጠሮአቸው ነባብያት፣ ለባውያን፣ ሕያዋን፣ ኃያላንም ናቸው። ሕማምና ሞት የሰባቸውም። የመላዕክት ቁጥር በአኃዝ አይወሰንም የብዙ ብዙ ናቸው።

ቅዱሳን መላዕክት የጌታ ስም በእነርሱ ላይ ስለሆነ ለመፀትም ለምህረትም ለበረከትም ይላካሉ። ቅዱሳን መላዕክት እግዚአብሔርን በማያቋርጥ ምስጋና ያመሰግኑታል በትንቢተ ኢሳ 6፥3 ላይ እንደተጻፈው "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እያሉ ይጮሁ ነበር" ያመሰግኑት ነበር።

"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ" ቀንና ሌሊት አያርፉም ራዕ 4፥8 መላዕክት በተፈጥሮአቸው ዘወትር የሚያመሰግኑ ጌታን የሚያከብሩ ናቸው። ምግባቸው መጠጣቸው ምስጋና ነው።

## 3.2 የቅዱሳን መላዕክት አገልግሎት

መላዕክት የእግዚአብሔርን ምህረት፣በረከት፣ ቸርነት ለሰው ልጆች፣ የሰው ልጆችን ጸሎት፣ ምህላ፣ ምዕዋት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡ የእግዚአብሔርና የሰው አገልጋዮች ናቸው።

⇒ "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን" ዕብ 1፤14.

- በእግዚአብሔር ፊት በባለሟልነት የሚቆሙ ናቸው። ሉቃ1፤19
- የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጽ የሚላኩ ናቸው። ኢያ 5፤13
- ለማዕታትን ከእሳት የሚያድኑ ናቸው። ዳን 3፤25
- የሰው ልጆችን የመዳን ቀን ቀድመው የሰሙና ይህንን ታላቅ የመዳን ምስጢር ያበሰሩ የእግዚአብሔር የምስጢር መዝገብ ናቸው። ሉቃ 1፤26
- የአዳኙን የመሲህ መወለድ ለሠው ልጆች ያበሰሩና በሰው ልጆች መዳን የተደሠቱ በጌታም ልደት ስብሐት ለእግዚአብር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብዕ ብለው የቀደሱ ናቸው ሉቃ 2፤8
- አዳኙን መሲን ለመግደል እነ ሔሮድስ ያጠመዱትን ወጥመድ ፈተው መሲህ ክርስቶስ ወደ ግብፅ እንዲሰደድ የተናገሩ ናቸው። ማቴ 2፤13
- መሲህ ክርስቶስ ከግብጽ እንዲመለስ የተናገሩ ናቸው። ማቴ 2፤19
- ጌታ ኢየሱስ አምላካዊ ጉዞውን ፈፅሞ ወደ መስቀል በሚወጣበት ሰዓት በእርሱ ላይ ሊፈርድበት ለተቀመጠው ለጲላጦስ አስደንጋጭ ቃል ነግሮታል። ይኸውም መንግስቴ በዚህ አይደለም መንግሥቴ በዚህ አለም ብትሆን ኖሮ ወደ አንተ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ(መላዕክት) ይዋጉልኝ ነበር። ዮሐ 18፤36
- እያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መልዐክ አለው። ማቴ 18፤10 ዳን 4፤1
- መላዕክት ትንሣኤውን ለሴቶች የነገሩ ናቸው። ማቴ 28፤3



- መላዕክት ክርስቶስ በቢታኒያ ተራራ ወደ አባቱ ሲያርግ ወደ ሰማይ እንጋጠው ይመለከቱ ለነበሩት ሐዋርያት ያጽናኗቸው ናቸው። ሐዋ 1፤10
- መላዕክት የጌታ ስም በነርሱ ሆኖ ሰዎችን የሚመሩ ወደ ርስት የሚያደርሱ ናቸው። ዘፀ23፤20
- በፍጻሜ ዘመንም ይህ ዓለም በሚያልፍበት ጊዜ ይላካሉ ኃጥአንን ከጻድቃን ይለያሉ ማቴ 24፤31 ራዕ 7፤1-4

በዚህ ሁሉ አገልግሎታቸው መላዕክት የእግዚአብሔርን ሕልውና ለምትገልጥ ቤ/ክርስቲያን ኃይል ድጋፍ ስለሆኑ ቤ/ክርስቲያን በአማላጅነታቸው ታመናለች።

## 3.3 የቅዱሳን መላዕክት ማዳንና አማላጅነት

✥ ዘፍ 48፤15 "ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን የመገበኝ እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልዐክ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ" የእግዚአብሔር መልዐክ አዳኝ ነው ይህም አዳኝነት በመጽሐፈ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታዎች የተነገረ ነው።

✥ መዝ 33(34)፤7 "የእግዚአብሔር መልዐክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል" መልዐክ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ እግዚአብሔርን በሚፈሩትና መልዐኩን በሚያከብሩት በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸዋል ብሎ የተናገረው ቅ/መላዕክት አዳኝ ስለሆኑ ነው።

✥ ዳን 10፤21 "ነገር ግን በእውነት ጽሁፍ የተፃፈውን እነግርሃለሁ በዚህም ነገር ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር ማንም የሚያጽናኝ የለም።" ቅዱሳን መላዕክት የሚያጸኑ የሚታደጉ መሆናቸውን ያሳያል።

✥ ዳን 12፤1 "በዚህም ዘመን ስለ ሕዝብም ልጆች የሚለቆም ታላቅ ሚካኤል ይነሳል። ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል። በዚህም ዘመን በመጽሐፍ ተጽፎ

የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል።" ቅዱሳን መላዕክት ለማዳን የሚንቀሳቀሱ ስለሆነ እግዚአብሔር በሰጣቸው ሥልጣን ያድናሉ።

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ብቻ ሣይሆን በአዲስ ኪዳንም በተለይ በሐዋርት ሥራ ላይ በተደጋጋሚ ቅዱሳን መላዕክት የተትረፈረፈ ሥራቸው የማዳን የመታደግ አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ እንመለከታለን። ጴጥሮስ ታስሮ በነበረ ጊዜ ሊታደገው ሊያድነው ፈጥኖ የመጣው የእግዚአብሔር መልዐክ ሰንሰለቱን ሰባብሮ ነፃ አውጥቶታል። ሐዋ 12፡7-11 እንዲሁ ጳውሎስና ሲላስ ታስረው በነበረበት ሰዓት የእግዚአብሔር መልዐክ ወረዶ አድኖአቸዋል። ሐዋ 16፡25-34 ይህ እያንዳንዱ የተመለከትናቸው በሙሉ ቅዱሳን መላዕክት ተራድያን ታዳጊዎች አዳኝ ስለሆኑ ዛሬም እየንዳንዳችን ከሚደርስብን ችግር ፈተና ውጣ ውረድ ከዚህ ዓለም መከራና ስቃይ ሁሉ ሊያድኑን ሲረዱን ሊያጽናኑን ይመጣሉ። ዘወትርም በረዳትነትና በአዳኝነት ይቆሙልናል።

### 3.3.2 የቅዱሳን መላዕክት ሥልጣን

✠ ዘፀ 23፡20 "በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ሥፍራ ያገባህ ዘንድ መልዐኬን በፊትህ እሰዳለሁ። በፊቱ ተጠንቀቁ ቃሉንም አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሰሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት" የእግዚአብሔርን መልዐክ ሥልጣን ነው የገለፀልን ባለሥልጣን ነው ለሚመስሉት ምህረት በማይመስሉት ላይ ቅጣት ማምጣት ይችላል። "ይቅር አይልምና" ያለው ሥልጣኑን ለማሳየት ነው።

✠ ሉቃ 1፡20 "ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም" አለው። የእግዚአብሔር መልዐክ ሊያበስረው መጣ እንጂ ዲዳ ሊያደርገው አልነበረም። ነገር ግን መልዐኩ ሥልጣን ስላለው ይህ እስኪሆን ዲዳ ትሆናለህ ብሎት ሔደ። ዘካርያስም ዲዳ ሆነ ይህ በመልዐኩ በራሱ ሥልጣን የሆነ ነው።



✠ 2ዜና 21፡30 "ዳዊት ግን የእግዚአብሔርን መልዐክ ሰይፍ ስለፈራ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወደዚያ ይሄድ ዘንድ አልቻለም።" መልዐኩ የሠራውን ሥራ ዳዊት ያውቅ ስለነበር የእግዚአብሔር መልዐክ ያለውን ሥልጣን ያይ ስለነበር መልዐኩ ወዳለበት ሥፍራ ለመግባት ፈርቶአል ይህም ዳዊትን ከመቀሰፍ አድኖታል

✠ 2 ጴጥ 2፡11 "ደፋሮችና ኩሮዎች ሆነው ሥልጣን ያላቸውን ሲሳደቡ አይንቀጠቀጡም ዳሩ ግን መላዕክት በኃይልና በብርታትም ከእነርሱ ይልቅ ምንም ቢበልጡ በጌታ ፊት በእነርሱ ላይ የስድብን ፍርድ አያመጡም።" መላዕክት ባለሥልጣኖች ኃያላን ናቸው። ግን ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ የሚያገለግሉ ስለሆኑ ዕብ 1፡14 እንዲመለሱ እንጂ እንዲጠፉ አይፈልጉም። እንደውም በሚመለስና እግዚአብሔርን ይቅር በለኝ ብሎ ንስሀ በሚገባ ከጥፋቱ በሚመለስ ሰው በነርሱ ዘንድ ደስታ ይሆናል። "ንስሀ በሚገባ ሰው ደስታ ይሆናል።" ሉቃ 15፡10

✠ ዘኍ 22፡33 "አህያይቱ አይታኝ ከፊቴ ሶስት ጊዜ ፈቀቅ አለች ከፊቴስ ፈቀቅ ባላለች በእውነት አሁን እንተን በገደልሁ እርስዋንም ባዳንኋት ነበር አለው።" የመግደልና የማዳን ኃይል ከእግዚአብሔር የተሰጠው ባለስልጣን ስለሆነ መሆን የሚገባውን ነገር ገና ትዕዛዝ የሚጠበት ሳይሆን በሥልጣናቸው ተገቢውን ነገር ያደርጋሉ።

✠ እንዲሁ ዘፍ 16 ላይ ለአጋር የእግዚአብሔር መልዐክ ውሃ ሲያፈልቅላት አናያለን።

### 3.3.3 የቅዱሳነ መላዕክት አማላጅነት

ከእግዚአብሔር ወደ ሰው ምህረትን፣ በረከትን፣ ፀጋን ይዘው እንደሚመጡ ሁሉ ከሰው ወደ እግዚአብሔርም ምልጃን፣ ፀሎትን ይዘው ይሄዳሉ፣ ያማልዳሉ። መላዕክት አገልግሎታቸው ከእግዚአብሔር ወደ ሰው፣ ከሰው ወደ እግዚአብሔር እየተላላኩ ማገልገል ስለሆነ ከተላኩበት

ከእግዚአብሔር በረከት ይዘው እንደሚመጡ ሁሉ ከሰው ወደ እግዚአብሔር ልመናን ይዘው ይሔዳሉ።

- ✞ ትን ዘካ 1፥12 "የእግዚአብሔር መልዐክ መልሶ አቤቱ የራዊት ጌታ ሆይ እነዚህ ሰባ ዓመት የተቈጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው አለ" ይህ ልመና ምልጃ የቀረበው ከእግዚአብሔር መልዐክ ወደ እግዚአብሄሐር ነው መልዐኩም ሰባ አመት ሙሉ በመከራ ለነበሩት ሕዝቦች ራርቶ ይቅርታ እንዲያደርግ ስለ ሕዝቡ ያቀረበው ፀሎት ነበር። እግዚአብሔርም በመልዐኩ ልመናና ምልጃ ይቅር ማለቱን አረጋግጦታል። ዘካ 1፥15-17 የእግዚአብሔር መልዐክ ለመነ አማለደ እንጂ ወደ ሰው ሲመጣ አናየውም ወደ እግዚአብሔር ግን አመለከተ።
- ✞ ሉቃ 1፥19 "እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ" እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ ያለው ጸሎትህን ያሳረጉልህ በአመላክ ፊት ጸሎትህ እንዲሰማ በአማላጅነቴ የረዳሁህ እኔ ነኝ ለማለት ነው። የምቆመው የሚለው ቃል ቀጥ ብሎ መቆምን ሳይሆን ለኛ የሚለምን፣ የሚያማልድ፣ የሚማፀን፣ የሚረዳ መሆኑን ያመለክታል አንዳንድ ማብራሪያዎችን እንመልከት።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እየመራ ወደ ምድረ ርስት እንዲወስዳቸው የታዘዘው ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ በእስራኤል ላይ እግዚአብሔር ቅጣቱን ሊያመጣ ሲል በርሱ ፊት ለምኖ ያስታረቀ ሙሴ ነበር። ለዚህም እግዚአብሔር ሲናገር እንዲህ ይላል "እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ።" መዝ 105(106)፥23 ባይቆም ኖሮ ያለው ቀጥ ብሎ ባይገተር ወይም ዝም ብሎ መቆምን የሚያመለክት አይደለም በመቅሠፍት ጊዜ እንዳይጠፋ በልመና ወደ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ በመማለድ ይጸልዩ ስለነበር ከመቅሰፈት ተርፈዋል። የእግዚአብሔር ቁጣ በነደደ ጊዜ ሕዝቡ እንዳይጠፋ ጸልዮ ያዳነው በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የቆመው ሙሴ



ነበር። "እግዚአብሔርም ሙሴን እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው። አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸውም እንዳጠፋቸውም ተወኝ አንተንም ስታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ አለው። ሙሴም በእግዚአብሔር ፊት ጸለየ አለም አቤቱ ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብጽ ምድር ባወጣው በሕዝብህ ላይ ስለምን ተቃጠለ… ከመዓትህ ተመለስ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ" ዘፀ 32፥9-12 ለዚህ ነው ሙሴ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያለው ስለዚህም "መቆም" የሚለው ቃል ምልጃን አማላጅ ሆኖ መገኘትን ያመለክታል። አንድ እንጨምር

- ✞ ዘፍ 18፥22 "ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ ወደ ሰዶምም ሔዱ አብርሐም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር" ዝም ብሎ መቆም ሳይሆን ሰዶምና ገሞራ ጻድቅ ቢገኝባት እንዳትጠፋ ሰመለመን ነበር። አብርሃም ለመነ ማለደ ግን የተባሉት ፃድቃን ሊገኙ አልቻሉም ቆሞ ነበር ያለው ለመለመን ለምልጃ መሆኑን ያመለክታል።

እንግዲህ ከዚህ በመነሳት "የምቆመው ገብርኤል ነኝ" ያለው ቃል አማላጅነትን የሚያመለክት ነው ስለዚህም ቅዱሳን መላዕክት የሚያማልዱን ስለእኛና ጸልየው ከጥፋት እንድንድን ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸው። ለዚህም ነው "ዘወትር የአባቶን ፊት ያያሉ" ሲል ጌታ የተናገረው ማቴ 18፥10

## 3.4 <u>ለቅዱሳን መላዕክት የሚደረግ የጸጋ ስግደት</u>

ቅዱሳን መላዕክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋ የተሰጣቸው እርሱ ያከበራቸው ስለሆኑ ስለ ጸጋቸውና ክብራቸው አምላካችን ናቸው ብለን ሳይሆን የእግዚአብር የሆኑትን ማክበር የተገባ ስለሆነ የጸጋ ስግደት እንሰግዳለን። እንኳንስ ኃያላን የሆኑትን መላዕክትን ቀርቶ እናትና አባትን ሰውን ሁሉ ማክበር እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

- ✞ "እግዚአብሔር የቀደሰውን ክቡር ብትሰው ከንቱ ነገር ከመናገር ተከልክለህ ብታከብረው በዚያን ጊዜ በእግዚአብር ደስ ይልሃል

በመድርም ከፍታበዎች ላይ እወጣሀለሁ።" ኢሳ 58፤13-14 ይህ ቃል የእግዚአብሔር የሆነውን የማክበር ምስጢር ይገልፅልናል። ስለሆነም እኛም እክብረን መስገዳችን ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስን እንመልከት

✞ ዘፍ 19፤1 "ሁለቱም መላዕክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ… ፊቱንም ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ" መስገድ የማይገባ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔር ሰው ሎጥ አይሰግድም ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሰው ሁሉን ያከብራል እንጂ ደፋር ስለላልሆነ እንዲህ ያለውን በእግዚአብሔር ቅዱሳን ላይ አመፃን አይናገርም አያደርግም። ስለሆነም የሎጥ ስግደት በፍቅር ነበር።

✞ ዘኁ 22፤31 "እግዚአብሔርም የበለዓምን ዐይኖች ከፈተ የእግዚአብሔርንም መልዐክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ አየ ሰገደም በግንባሩ ወደቀ" ስለ መልዐኩ ክብር ሰገደ ተደፋ። በለዓም መልዐኩን በመፍራት ሰገደ። ስለ ፍቅር የሚሰግድ አለ በመፍራትም የሚሰግድ አለ በዚያም ሆነ በዚህ ግን ለቅዱሳኑ መላዕክት ስግደት የሚገባ ስለሆነ እንሰግዳለን።

✞ ኢያ 5፤14 "ኢያሱም ወደ ምድር በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድን ነው አለ" ኢያሱ በአጠገቡ ቆሞ ስለነበረ የእግዚአብሔር መልዐክ ክብር ሰገደ የማይገባ ቢሆን ግን ባልሰገደ ነበር።

✞ ሐዋ 27፤23 "የእርሱ የምሆንና የማመልከው የእግዚአብሔር መልዐክ በዚች ሌሊት በአጠገቤ ቆሞ ነበር…" እንደውም ጳውሎስ የማመልከው ሲል ገልጸለታል በእንግሊዝኛውም እንዲህ ይላል "For last night an angel of the God to whom I belong and whom I worship come to me" Act. 27፤23 የማመልከው ማለቱ ፈጣሪ የሆነ ማለቱ ሳይሆን የምሰግድለት የእግዚአብሔር መልዐክ ማለቱ ነው የሚያማልደኝ የማከብረው



የእግዚአብሔር መልዐክ ማለቱ ነው። እንግዲህ ልብ ላለውና ማስተዋል ለሚፈልግ ሰው ይህ በቂው ነው።

### 3.4.1 ለቅዱሳን መላዕክት ስግደት አይገባም የሚሉበት ጥቅስ

☞ ራዕ 19፤9-10 "እርሱም ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዐን ናቸው ብለህ ፃፍ አለኝ። ደግሞም ይህ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ነው አለኝ።" ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ እርሱም እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሄጠር ሰገድ የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ"

☞ ራዕ 22፤8-9 "ይህንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልዐኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። እርሱም እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህን መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁት ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሄር ሰገድ አለኝ።"

እነዚህ ሁለቱ ጥቅሶች በራዕይ ዮሐንስ ላይ በተለያየ ምዕራፍ የተፃፉ ናቸው ብዙ ጊዜ እነዚህን በመጥቀስ ለማሳመንና ለመላዕክት ሰግደት አይገባም ለማለት ይሞክራሉ። ነገር ግን ሁለቱም ጥቅሶች ላይ መልዐኩ ስለ ትህትና የተናገረው መሆኑን እናስተውላለን። ቅዱሳን መላዕክት ከእምላካቸው እንዳዩት ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ሲገልጡ እናያለን ለምሳሌ ከእረኞች ጋር ዘምረዋል። ሉቃ 2፤13 እንዲሁ መልዐኩ ከሁሉ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ እላለም ከአንተ ጋር ብሉታል ዮሐንስ ማን ነበር? የሚል ጥያቄ እንስተን ማንነቱን እንድናውቅ ያስገድደናል።

ዮሐንስ ሐዋርያ (ፍቁረ እግዚእ) ሱታፌ ቅዱሳን የደረሰ ወይም ከቅዱሳን መላዕክት እንድነት የደረሰ ቅድስና ያለው ሰው ነበር። ስለዚህ መልዐኩ

በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ክብሩን ስለሚያውቅ ከአንተ ጋር ባሪያ ነኝ አለ። ከወንድሞችህ ከነቢያት ጋር አለ ይህን የሚሉ እነርሱ ነቢያት ናቸው ወይ ከነቢያት ሲል ትንቢቱ ተሰጥቶአቸው በፍጽምና የእግዚአብሔር አገልጋዮች ጋር ማለቱ ነው። የዚህን መጽሐፍ ቃል ከሚጠበቁ ጋር ይላል ይህን የሚሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ይጠብቃሉ ወይ? መልዐኩ የመጽሑን ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ሲል አገልጋይ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይኸውም ትህትናን ለማሳየት የተናገረው ነው። ይህችን ቤ/ክርስቲያን ለመቃወም የተነሱ በሙሉ ትዕቢታቸው እጅግ የከበደ የራሳቸውን ማንነት በትክክል የማያውቁ ደፋሮች ስለሆኑ እነርሱ እንደሚያስቡት ከሁሉ ጋር እኩል ናቸው። 2ጴጥ 2፤1-13

ስለዚህ ክርስቲያኖች እኛ እርስ በርሳችን እንድንከባበር ያስተማረን ጌታ አንዱ ሲመጣ የተቀመጠው ብድግ ብሎ ሊያስቀምጠው ሲል ስለ ትህትና እንዳታደርገው እንደሚለው ሁሉ መልዐኩም ሁለት ጊዜ ያለው ትህትናን ለማሳየት ነው። ዮሐንስማ ተደፍቶ ለግዶአል ስግደቱ ተከናውኗል ግን የትህትና ሕይወት ለማሳየት ነው። ራሱን ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳልና ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል። እንዳታደርገው የሚለው ቃል መልዐኩ ስግደት እንዳይፈጽምለት የተከላከለበት ሳይሆን የዮሃሐንስን ክብር የሚያሳይ ነው። እንዲህ ባይሆንማ ቀድሞ ሲሰግድ ያየናቸው ሁሉ ባልሰገዱ ነበር። የእግዚአብሔር ሥራ በዘመናት አይለዋወጥም። ሚል 3፤6



# ምዕራፍ አራት

## ቅዱሳን

ቅዱሳን የሚለው ቃል በግዕዝ ንጹሕ ልዩ መሆንን የሚያመለክት ነው። ይህ ቃል ለእግዚአብሔር የባሕርይ መግለጫ ነው። እግዚአብሔር በባሕርዩ ቅዱስ ነውና ቅድሳን የሚለውንም ቃል በባሕርዩ ቅዱስ የሆነውን አምላክ ሊያገለግሉ መላዕክትና ደጋግ ሰዎች የሚሰጥ ነው።

መላክትን ቅዱሳን እንላቸዋለን ከማንኛውም ክፉ ነገር የራቁ ሥርዓታቸውን የጠበቁ እግዚአብሔርን ያወቁ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ስለሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ። ከመዓረግ መላእክት የደረሱ ደጋግ ሰዎችም በዚሁ የቅድስና ስም ይጠራሉ፣ ራሱ እግዚአብሔር "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ዘሌዋ 19፤2 1ጴጥ 1፤15-16

ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት ሁሉ ለቅዱስ እግዚአብሄር ሲሉ ሕይወታቸውን መስዋዕት አድርገው ስለሰጡ፣ ለስሙ ስለ መሰከሩ፣ በተጋሉአቸውና በትሩፋታቸው ስላገለገሉ የቅድስናና የብፅዕና ማዕረግ ተሰጥቶአቸዋል፣ ይሰጣቸዋልም ጌታችንም በወንጌል "አባት ሆይ በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ ቅዱስ ነው" ብሎ ስለቅድስናቸው ተናግሮአል። ዮሐ 17፤17

### 4.1 ቅዱሳን በገድል በሶስት ይከፍላሉ

1. በአላውያን (በማያምኑ) ነገሥታት ፊት ስለ ክርስቶስ አምላክነት ሳያፍሩ፣ ሳይፈሩ መስክረው እስከ ደም ጠብታ ድረስ ለክርስቶስ የመሰከሩ ሰማዕታት ናቸው። ሰማዕት ማለት መስካሪዎች ማለት ነው።

ለምሳሌ፦ ቀዳማዊ ሰማዕት ቅ/እስጢፋኖስ፣ መርቆሬዎስ፣ ቅ/ቂርቆስ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሐዋ 7፡55 ራዕ 12፡11 "እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምሥክራቸው ቃል የተነሣ ድል ነሡት ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።"

2. በገዳል በዱር በዋሻ ሆነው ከሥፋው ዓለም ተለይተው ክረስቶስ ለሞተለት ለዚህ ዓለም ሲጸልዩ ግርማ ሌሊቱን፣ ድምፅ አራዊቱን፣ ጸብዓ አጋንንትን ታግሠው የሚኖሩ ፃድቃን ናቸው። ለምሳሌ፦ ፃድቁ ተ/ሃይማኖት፣ ፃድቁ ገ/መንፈስ ቅዱስ።

3. መጽሐፍ አውጥተው፣ አንቀጽ አልበው፣ መናፍቃንን ተከራክረው የቤ/ክ ሕልውና ያስከበሩ የቤ/ክርስቲያን ጠበቆች /አፖሎጂስቶች/ ናቸው። ለምሳሌ፦ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቄርሎስ፣ ጎርጎርዮስ፣ ባስልዮስ ወዘተ

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቅድሳን ማክበርና መቀበል እርሱን ማክበር መሆኑን ገልጦልናል። ማቴ 10፡40, ሉቃ 10፡16 ቅዱሳን ሰዎች ያከበረ እግዚአብሔር ነው። እርሱ ያከበረውን ደግሞ መናቅ አይገባም መጽሐፈ ቅዱስ ክበራቸውንና በእርሱ ዘንድ ያላቸውን ተሰሚነት በብዙ መልኩ ገለጦአል። ይህ ብሉይ ኪዳን ነው አዲስ ኪዳን ነው የምንለው ሳይሆን በማንኛውም ኪዳን ውስጥ ጌታ ያከበራቸውን ቅዱሳን ማየት ይገባል። ሁላችንም ወደ መልካሙ የእግዚአብሔር አሠራር ብንመጣ እግዚአብሔር ሊቀድሰን ፈቃዱ ነው። ለዚህም ነው "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ያለን። ዘሌ 19፡1 እያንዳንዳችን ለቅድስና ተጠርተናል ይህ ማለት ግን መናፍቃኑ እያንደሚያስቡ ሌሎቹ ምን ያደርጉልናል እያሉ በትዕቢት እንደሚናገሩት አይደለም የእያንዳንዳችን መጠራት ለበጎ ለመልካሙ የእግዚአብሔር ሥራ ነውና።

## 4.2 የቅድሳን ክብርናግ አማላጅነት

- ዘፍ 18፡17 "እግዚአብሔር አለ እኔ የማደርገውን ከአብረሃም እሰውራለሁን?" እግዚአብሔር ስላላቸው ክብር ሲል ትዕዛዙን ለፈጸሙ፣ ለወደዳቸው ቅዱሳን ሳይሰውር ሁሉን ገልጦላቸዋል። አብርሃም የሰዶምና ገሞራ መጥፋት በተነገረው ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ። ቆመ ማለት ማለደ፣ ተማጸነ ማለት መሆኑ ግልጽ ነው። ምክንያቱም በዘፍ 18፡22-33 እግዚአብሔር እንዲምር ፃድቃን ቢገኙ ይቅር እንዲል ሲማፀን ሲለምን እናያለንና።

- ዘፍ፡20፡7 "አሁንም የሰውየውን ሚስት መልስ ነቢይ ነውና ስለ አንተም ይጸልያል ትድናለህም "እግዚአብሔር ስለ ወዳጁ ስለ አብርሃም የተናገረው ነው። አቤሚሌክ ሚስቱን በወሰደ ጊዜ እግዚአብሔር ቀጥቶ አቤሜሌክ ሚስቱን እንዲመልስ አድርጎታል። ስለ ወዳጁ አብርሃም ክብር ገልጦለታል። መዳን ቢፈልግ እንዲሁ እንዲፀልይለት ነግሮአል።

- ኢዮ 42፡7-11 "አሁንም ሰባት ወይፈንና ሰባት ዳንግላ ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ሂዱና ስለ እናንተ የሚቃጠለውን መስዋዕት አሳርጉ።" ኢዮብም ስለ እናንተ ይጸልይላችሁ ጸሎቱን እቀበላለሁ" አስተውሉ እነርሱ ቢጸልዩ አልቀበል አላቸው ይህም የወዳጁን ኢዮብን ክብሩን ለመግለጽ ነው። እርሱም ስለ እነርሱ ጸለየ እግዚአብሔርም ይቅር አላቸው።

- ዘፀ 32፡7-15 "እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት እነሆም አንገተ ደንደና ሕዝብ ነው። አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ" በዚህ ሰዓት ሙሴ ወደ እግዚአብጤር ጮኽ አስተምሮአቸዋል። ለዚህም በመዝ 105፡23 ላይ "በፊቴ ሙሴ ባይቆም ኖሮ አጠፋቸው ነበር" ብሎአል ባይቆም ማለቱ ባይለምን ባያማልዳቸው ኑሮ ለማለት እንደሆነ ግልጽ ነው።

- ኤር 12፡2-13 ስንመለከት ኤርምያስ ለሕዝቡ ጸለዮ ,በ10 ቀን ጸሎት ምሕረትን ሲያሰጣቸው እናያለን። እኛ ራሳችን እንለምን ምን ይከለክለናል? አላሉም።

እንዲህ ያለው አገልግሎት በብሉይ ብቻ ሳይሆን በአዲስ ኪዳንም አለ። ለእግዚአብሔር አምላክ "ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደርጋለሁ" እንዳለ መዝ 88(89)፡3 ቃል ኪዳን ከቅዱሳን ጋር አለው ለዚህም ነው ጌታ በሉቃ 10፡16 እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ እናንተን የጣለ እኔን ጣለ ያለው በአዲስ ኪዳን በማቴ 15፡21 ጀምሮ ስንመለከት የከነናዊቷን ሴት ጩኸት እንዲሰማ ሐዋርያት ስለጠየቁት እርሱም ስለ እምነቷ ስለ ሐዋርያቱ ጥያቄ ልጇን አድኖላታል።

መጽሐፍ በዕብ 5፡16 "የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" ይላል። ስለዚህም ጻድቅ ሰው ቅዱስ ሰው ልመናው ቅድመ እግዚአብሔር ይደርሳል። ግዳጅም መፈጸም ይቻላታል። በአዲስ ኪዳን በወንጌል ሰዎች ስለሌሎች እየለመኑ ሲያስምሩ እንመለከታለን። የሚከተሉትን ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ተመልከት።

| | | |
|---|---|---|
| 1. ማቴ 8፡5 | 6. ማር 2፡3 | 11. ሉቃ 9፡35 |
| 2. ማቴ 9፡2 | 7. ማቴ 7፡25 | 12. ሉቃ 7፡2 |
| 3. ማቴ 15፡22 | 8. ማቴ 8፡22 | 13. ዮሐ 4፡46 |
| 4. ማቴ 15፡22 | 9. ማር 9፡17 | 14. ዮሐ 11፡3 |
| 5. ማቴ 17፡14 | 10. ሉቃ 5፡18 | 15. ሐዋ 9፡36 |

በእነዚህ ጥቅሶች የምናረጋግጠው የምልጃ ሥራ አሁንም እንዳለ ነው። የእነዚህ ሰዎች ጸሎት ልመናቸው በእግዚአብሔር ፊት ከተሰማ የፃድቅ ሰው ጸሎትማ ምን ያህል ኃይል ይኖራት ይሆን። እግዚአብሔር ስለ ቃል ኪዳኑ አይዋሽምና "እግዚአብሔር ይወሽ ዘንድ ሰው አይደለም" ይለናል። ዘኁ 23፡19

ጌታ እንደተናገረው "በእኔ የሚያምንብኝ ቢኖር እኔ የማደርገውን ብቻ ሳይሆን ከዚ የበለጠ ያደርጋል።" ዮሐ 14፡12 እንዳለው ቅዱሳን ጌታ የሚሰራውን ከሱ ይበለጥ የሚያደርጉ ከሆነ በዚህ ዓለም በወዲያኛውም



አለም እንዴት ማማለድ አይችሉም? ደግሞስ መጽሐፍ ቅዱስ አይደለም ማማለድ ለቅዱሳን የአማልክትነት ማዕትም በጸጋ አምላክ እንደሆኑ ሲናገር እናያለን ለምሳሌ ሙሴን በፈርኦን ላይ አምላክ አድርጌአለሁ ሲል እናነባለን ዘፀ7፡1 እንዲሁ በመዝ 81(82)፡6 "እኔ ግን አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ ነገር ግን እንደሰው ትሞታላችሁ" ብሎ ሲናገር ለቅዱሳን አይደለምን? መጽሐፍ ቅዱስ አማልክት እስኪባሉ ክብር እንዳላቸው ይናገራል ለዚህ ነው ሙሴን በፈርኦን አምላክ አድጌሐለው ያለው ዘፀ 7፡1 ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ በዮሐ. 10፡34 ላይ "የእግዚአብሔር ቃል የመጣላችሁ አማልክት ካላችሁ ይላል ታዲያ ቃሉ የመጣላቸው ቅድሳን አይደሉምን? ይህ በርሱ ዘንድ ያላቸውን ክብር የሚያሳይ ነው። አንዳንዶች ይህ የማይዋጥላቸው እኔም እኮ ቃሉ መጥቶልኛልና አማልክት አባላለሁ ብለው በድፍረት ሲናገሩ ይደመጣሉ። እነዚህ ሰዎች መጨረሻቸው ጥፋት ነው እንዳለ ፊል. 3፡21 ለጥፋትና ለጠማማነት እንዴት ሰይጣን ስላስነሣቸው እርሱ በወደቀበት ትእቢት ዛሬ ብዙዎችን ይፈትናቸዋል፣ ይጣላቸዋልም። እነዚህ ሐሰተኞች ናቸው ራሳቸው ይለወጣሉ ብሉአልና። 2ኛ ቆሮ.11፡15-17 እግዚአብሔር እንዲህ ካለ ድፍረት ያውጣን።

2ጴጥ 2፡19 "ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ከዓለም ርኩሰት ካመለጡ በኋላ ዳግመኛ ለእርስዋ ተጠላልፈው የተሸነፉ ቢሆኑ ከፊተኛው ኑሮአቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል።

2ጴጥ 3፡3 "መጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ"

### 4.2.1 ከሞቱ በኋላ በአጸደ ነፍስ ማለት

- 2ኛ ቆሮ 9፡4 "ራሳቸውም ስለ እናንተ ሲያማልዱ ከሚበለጠው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ይናፍቁአችኋል" ቅዱሳን የማማለድ ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ተቀብለዋል።
- 2ኛ ቆሮ 5፡20 "እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።" እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ቅዱሳን ሊያማልዱ እንደሚችሉ የሚያሳየን ነው።

ስለማማለድ በተነሳ ቁጥር ሰው በሥጋ በሕይወት እያለ ያማልዳል ከሞተ በኋላ ግን አያማልዱም ይላሉ። ሰው በምድር ሲኖር ሥጋና ነፍሱ ተዋህደው ያለ ፍጡር ነው እግዚአብሔርን ማክበር፣ መውደድ፣ ሕጉን ትዕዛዙን መፈጸም የነፍስ ተግባር ስለሆነ ዳዊት በመዝሙሩ ነፍሱ ወደ እግዚአብሔር እንደምታመለክት ያናገራል። በሉቃ 1፡42 ላይ "ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች" ስትል ድንግል ማርያም ትናገራለች። እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው ነፍስ የማትሞት በመሆኗ እግዚአብሔር የመረጠውን በጎ ሥራ ትሠራለች ሥጋን ቀጥታ የነፍስ ሥራ ታሰራዋለች። በገላ 5፡17 የሥጋ ሥራ የተገለጠ ነው ብሎ ሥጋ ምን እንደሚሠራ ተናገሮናል። ሥጋ ከነፈስ በልጦ ሕይወት አይባልም ሥጋ ሟች በሰባሽ ነው ወደ አምላክ ዘንድ የምትቀርብ ነፍስ ነች ይህን ሁሉም ይስማማበታል። እንግዲህ አንድን ሰው ሰው አሰኝቶ ያኖረው የሁለቱ ውህደት ቢሆንም ሕይወት አለው ያሰኘው ነፍስ በመኖሯ ነው። ስለዚህ እነዚህ እነዚህ ቅዱሳን በምድር ሲኖሩ የነፍስ ሥራ ይሰሩ ነበር። እንዲ ቢሞተም አገልግሎት አይቋረጥም ታላቅ ዋጋ ያለው ነፍስ እንጂ ሥጋ አይደለምና፤ በሚሞተው ሥጋ ሚሆን በማትሞት ነፍስ መኖር ታላቅ ነውና ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ" ያለን ሥጋ ፈራሽ ነውና ስለዚህም ጌታ "እኔ የሕያዋን አምላክ



እንጂ የሙታን አይደለሁም" ብሉናል ማቴ 22፡32 ስለዚህም የሕያዋን አምላክ ከሆነ ከሙታን ጋር ሕብረት የለውም ሙታን የሚባሉት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስረዳን በምድር ሲኖሩ እግዚአብሔር ያልተደሰተባቸው እምነት የሌላቸው ናቸው "ሙታናቸውን እንዲቀበሩ ሙታንን ተውአቸው" ሉቃ 9፡60 የቆሙትም ሙታን ነበሩ የሞቱም ሙታን ነበሩ። ሙታን ያሰኛቸው በእምነት ያልኖሩ ምግባር የሌላቸው የማያስደስቱ ስለሆኑ ነው።

ቅድሳን ግን ሙታን አይባሉም የእግዚአብሔር ናቸውና የእርሱን ፍለጋ ተከትለው የኖሩ በእርሱም የጸኑ ናቸውና "የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና" 1ኛ ጴጥ 2፡21 ለዚህም ነው "ነፍሳቸውን እስከሞት ድረስ አልወደዱም" ሲል ራዕ 12፡11 ላይ የተናገረን ቀደም ብለን እንደገለጽነው እነርሱ ከሚበልጠው ጸጋ የተነሣ ይናፈቁአችኋል እንዳለ የእግዚአብሔር ጸጋ በኛ ላይ ይወርድ ዘንድ ስለእኛ እንደሚያማልዱ ያረጋገጥልን ለዚህ ነው 2ቆሮ 9፡14። ፍለጋውም ሁላችንም እንድን ዘንድ ነውና እግዚአብሔር በጥቂት ምክንያት ሊያድነን ፈቃዱ ነውና፤ቃሉም "ዓለምን ሊያድን እንጂ በዓለም እንዲፈርድ ልጁን አላከውም" ያለው ለዚህ ነው ዮሐ 3፡20 ከዚህ በመነሣት የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመለከት ቅዱሳን በእግዚአብሔር ዘንድ ሕነያው ሆነው ፍርድን፣ ድህነት ነፍስን ለሰው ልጅ ይሰምናሉ። ያማልዳሉ።

- ማቴ 10፡41 "ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቅን ዋጋ ይወስዳል ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም" ይህ መንታሰቢያ ለሚያደርግ ሁሉ ዋጋው አይጠፋም ያለው ቅድሱ ሰው በስጋ ቡሞት ህያው ነውና የማይጠፋ ዘላለማዊ ክብርና ፀጋ እንዳለው

ያመለክታል። ዋጋው ያልጠፋውን የሰጠውን ቅድስ ሰው ዘወትር ስለእግዚአብሔር ቃለኪዳን ሲል ይፀልያል ይማልዳል።

- ራዕ 6፡9 "...ቅዱስ እውነተኛ ጌታ ሆይ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንም በምድር በሚኖሩ ላይ አትበቀልም አሉ..." እግዚአብሔርን ፍርዱን የሞቱ ሰዎች ነፍሳት ሲጠይቁት የምናይበት ነው። በነፍስ ፍርድን መለመን እንዳለ ሁሉ ምልጃን ይጠይቃሉ።
- ሉቃ 16፡31 ስለ ነዌና አልዐዛር ስንመለከት ነዌ በሲኦል በስቃይ ሳለ ለወንድሞቹ በምድር ለሚኖሩት ሲለምን እናየዋለን። እግዚአብሔር እንኳንስ ለቅዱሳን፣ ለፃድቃን አይደለም በሲኦል ሆኖ ለወንድሞቹ ለለመነው ሰው ተገቢውን መልስ እንደሰጠ ይልቁንም በፀሎት በኃይል ያላቸው የእግዚአብሔር ቅዱሳንማ በእርሱ ዘንድ መለማታቸው ምን ያህል የገነነ ይሆን? ስለዚህ በነፍስ ያሉ ቅዱሳን ሰዎች ነፍሳት እንደሚለምኑ በቀላሉ ልንረዳበት የምንችልበት ነው። ልብን አጠንክሮ የእግዚአብሔርን አሰራር ከመቃወም እውነቱን እያዩ በማስተዋል መኖሩ ይሻላል። መናቅን፣ ትዕቢትን አስወግዶ ራስን ዝቅ አድርጎ መቅረብ እንጂ ንቀተና ትዕቢት በቅዱሳን ላይ የሚናገር የማን እህሉን ንግግር የትም አያደርስም መጨረሻውም ጥፋት ነውና እንጠንቀቀ እንላለን።

እንዲሁም የሞቱት ሰዎች አፅማቸው ራሱ ድንቅ ተአምራትን ሲሰራም እንመለከታለን 1ኛ ነገ 13፡31 ተመልከት።

## 4.3 ቅዱሳን አያማልዱም የሚሉበት ጥቀስ ትንታኔ

- መክ 9፡4 "ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላልና ሰው ከሕያዋን ሁሉ ጋር ቢኖር ተስፋ አለው ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉና ሙታን ግን አንዳች አያውቁም መታሰቢያቸው ተረስቶአልና ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም" ይህን ጥቅስ ስንመለከት በደንብ ሊተነተን ይገባዋል ምን ማለት እንደሆነ እያንዳንዱን እየዘረዘርን እንመለከተዋለን።



አስቀድሞ ይህ ጥቅስ ለምንና ለማን እንደተነገረ ባለማስተዋላቸው ራሳቸውን ያሉ በሕይወት የሚገኙ ውሾች ቅዱሳንን የሞቱ አንበሶች አድርገው እኛ ከነሱ እንሻላለን ሲሉ መደመጣቸው ፍጹም እግዚአብሔርን የሌለበት እምነት ውስጥ እንዳሉ የሚያሳይ ነው። እኛ እናውቃለን እነሱ አያውቁም የሚለው አገላለጽ ከክርስትና ውጭ የሆነ ነው። ይህም ትዕቢት ፈጽሞ የሚጥል ነው። ነገር ግን በመከከላቸው በትህትና የኖረ አባት ስለሌላልቸው በአመፅ ሲኖረሩ የማያፍሩት፣ የማይፈሩት ለዚህ ነው። ከሁሉ በፊት ግን ትህትና ትልቅ ገንዘብ ሊሆን ይገባዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ታላላቅ ሰዎች ራሳቸውን በትህትና ዝቅ ያደረጉ እንጂ እንዲህ ዓይነት ድፍረት ሲናገሩ ታይቶ ተሰምቶ አይታወቅም።

"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሁታን ግን ጸጋንግ ይሰጣል እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተ ይቀርባል።" ያዕ 4፡6 በማለት ራሳችንን አዋርደን ማቅረብ እንዳለብን ይነግረናል። ነቢዩ እግዚአብሔር ልበ አምላክ ዳዊት "የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም" ያለው ለዚህ ነው። መዝ 50፡17

የእምነት አባት የነበረው አብርሃም በዘፍ 18፡27 "እኔ አፈርና አመድ ነኝ" ሲል ራሱን ዝቅ አድርጎ ተናገረ እንጂ ራሱን ከፍ በማድረግ አንዳች አልገለጸም። እንዲሁ ዳዊት በመዝ 21፡6 ላይ "እኔ ግን ሰው አይደለሁም ትል ነኝ" ብሏል። በአዲስ ኪዳን ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 15፡8-9 ላይ "...ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና" በማለት ራሱን አሳንሶ ገለጠ እንጂ እበልጣለሁ እሻላለሁ አላለም። እዚህ ላይ አንሳለሁ ያለው በሕይወት ካሉት እንጂ መቼ በአፀደ ነፍስ ካሉት ጋር አለ? እንዳይባል ታላቁ የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነውና የሞትን ጽዋ ሳይቀምስ በእሳት ሠረገላ ወደ ሠማይ የወጣው ኤልያስ በ1ኛ

ነገ 18፥14 ላይ "ይበቃኛል አሁንም አቤቱ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ" ብሎ ራሱን በሥጋ ከእርሱ ቀድመው ከነበሩ አባቶቹ አሳንሶ ተናገረ እንጂ አበልጣለሁ አላለም።

እንግዲህ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የትዕቢት ንግግር እንደሆነ እናስተውላለን።

፫

⇒ ያልሞተ ውሻ፦ ይህ ቃል የተነገረላቸው ሕይወታቸውን እየተው ኃጢአተኝነታቸውን አውቀው የሚጸጽታቸው፣ የሚቆረቁራቸው፣ ዘወትር የእግዚአብሔርን ቸርነት፣ ታጋሽነት፣ መሃሪነት፣ ይቅር ባይነት እያሰቡ በቃሉ ሕይወታቸውን ለንስሐ አዘጋጅተው ወደ እርሱ የሚቀርቡትን ኃጢአተኞች ነው። ያልሞተ ውሻ የተባሉት በሕይወተ ሥጋ ያሉ ኃጢአተኞች ናቸው። ይኸም ከላይ የጠቀስናቸው አይነት እንጂ ሁሉን አይደለም።

ኃጢአተኞች በውሻ ይመሰላሉ። ለዚህም ነው ጌታ በሚያስተምርበት ሰዓት ከነናዊቷ ሴት የተቀደሰውን ለውሾች መስጠት እንደማይገባ ሲነግራት ቡችሎች ከጌቶቻቸው ፍርፋሪ አዎ ይበላሉ ብላ የተናገረችው፣ ጌታም ማንነቷን አውቃ ኃጢአተኛ እንደሆነች ተረድታ ምህረትን በመፈለጓ አልከለከላትም የምትሻውን አድርጎላታል ማቴ 15፥21-28

እንዲሁ ጴጥሮስ በመልዕክቱ አውቀው ወደ ስሕተት ስለተመለሱ ሲናገር "ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል ደግሞ የታጠበች እርያ ወደ ጭቃ ለመንከባለል ትመለሳለች እንደሚባል እውነተኛ ምሳሌ ሆኖባቸዋል።" 2ኛ ጴጥ 2፥22 ውሾች የተባሉ ንስሀ ለመግባት ጊዜ የተሰጣቸው በዚ ምድር ያሉ ኃጢአተኞች ናቸው። በሮሜ 2፥3-5 እንደተገለጸው "ልብህን አጠንክረህ ንስሀ ባትገባ የእግዚአብሔርን ቁጣ በራስህ ላይ ታከማቻለህና" ሲል የተናገረው። "ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉ" ሲል የገለጸው ነገ እንሞታለን ብለው እንደ ደገኛ አባቶች ኃጢአታቸውን ተናዘው ይቅር ተብለው እንዲሞቱ ያውቃሉ።



ሲል የገለጸው ነገ እንሞታለን ብለው እንደ ደገኛ አባቶች ኃጢአታቸውን ተናዘው ይቅር ተብለው እንዲሞቱ ያውቃሉ። ያዕቆብ "አሁን ታይቶ እንደሚጠፋ እንፋሎት ነን" ያዕ 4፥14 የተናገረው እነዚህ በሕይወተ ሥጋ ያልሞቱ እንዲሞቱ አውቀው ወደ ንስሀ ሊመጡ ይችላሉና ነው።

⇒ የሞተ አንበሳ፦ የተባሉ ደግሞ ንስሀ ሳይገቡ በሠሩት ኃጢአት በክፋ ስራቸው ተጸጽተው እግዚአብሔርን ይቅርታ ሳይጠይቁ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን ኃጢአተኞች ነው። ይኸውም በምድር ሲኖሩ ለሥጋ ፈቃዳቸው ብቻ ኖረው በዝሙት፣ በርኩሰት፣ በጣኦት ማምለክ፣ በቁጣ፣ በአመፃ ኑረው የሞቱ የኃጢአት ሥራ አንበሶች የነበሩ፣ በምድር ሲኖሩ ሰው አስጨንቀው ደም አፍስሰው የወደዱትን ሰርተው የኖሩ ናቸው እነዚህ ሞታቸው እንኳ በርሱ ዘንድ የከፋ ነው። ዘሌ 26፥1 ኢሳ 5፥11-12 ኤፌ 5፥3-6 ገላ 5፥16-21 ቆሮ 6፥9

ጻድቃን ቅዱሳን ግን እግዚአብሔር "ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር" የጻድቅ ሰው ሞቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ ነው መዝ 115፥6 ብሎ ተናግሯል። የጻድቃን ቅዱሳን ሞት የሞቱ አንበሶች ከተባሉ ከኃጢአተኞች ጋር የሚታይ አይደለም። የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት ክቡር ነው እንጂ። ጳውሎስም ሲናገር እነሱ የሄዱበት የተሻለ እንደሆነ ሲናገር እንዲህ ብሎአል። "ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና" ፊል 1፥23 ቅዱሳን በዚህ ዓለም ከሚኖራቸው ሕይወት ይልቅ ሰማያዊው ሕይወታቸው የበለጠ እንደሆነ ተናግሯል። ለዚህም ነው "ሩጫዬን ጨርሻለሁ የድል አክሊል ይጠብቀኛል" ያለው።

ለምን በአንበሳ ተመሰሉ ብለን እኒያ የሞቱ ኃጢአተኞች የግብር አባታቸውን ዲያብሎስን ይመስላሉና በ1ኛ ጴጥ 5፥6-8 እንደምናነበው "...ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን እንደሚፈልግ አንበሳ በዙሪያችሁ ያናፋልና" በማለት ገልጾታል። ኃጢአት አድርገው ንስሀ ሳየገቡ የሞቱት ኃይለኞች በሞተ አንበሳ የተመሰሉት ለዚህ ነው። በዮሐ 8፥39 "እናንተ

ከአባታችሁ በዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁን ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ... ሐሰተኛ የሐሰት አባት ነውና" ብሏል። ስለዚህ የዲያብሎስን ፈቃድ የሚፈጽሙ የግብር ልጆቹ በሚያገሳ አንበሳ የተመሰለው ዲያብሎስ አድሮባቸው በደል ሲያሰራቸው ኑሮ ንስሀ ሳይገቡ ሞተዋልና።

እንግዲህ "ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላልና" ያለው ያልሞቱ ኃጢአተኞች ንስሀ ለመግባት ጊዜ አግኝተው ይቅርታ ጠይቀው ንስሀ ገብተው ምህረትን ለማግኘት ይችላሉና 2ጴጥ 3፥8-10 ነገር ግን የሞቱ የተባሉ በክፋታቸው አንበሳ ኃይለኞች የነበሩ ሞተዋልና ወደ ንስሀ መመለስ ስለማይችሉ ያልሞተ ውሻ ከሞተ አንበሶ ይሻላል ያለው ለዚህ ነው።

⇒ ሰው ከሕያዋን ጋር በአንድነት ቢኖር ተስፋ አለው ያስኘው ሕያው አምላክ እግዚአብሔር ሕያዋን ካደረጋቸው ቅዱሳን ጋር ቢኖር የመዳን ተስፋ አለው። በመክ 9፥3 ላይ እንደተጠቀሰው ልቡ በክፋት ተሞልታ ወደ ሞት ከመውረድ ሊያተርፈው የሚችለውን ንስሀ የማግኘት እድል አለ። አንድም ቅዱሳን ሕያዋን ናቸውና በእርሱ ሕይወትና ኑሮ እምነት ቢመላለስስ ተስፋ አለው ለማለት ነው። ይህን በሚከተለው ጥቅስ እንመልከት

- "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" 1ቆሮ 11፥1
- "የእግዚአብሄርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ ...በእምነታቸው ምሰሉአቸው" ዕብ 13፥8 እነዚህ ከላይ ያየናቸው ጥቅሶች ሰው ሕያዋን ከሆኑ ቅዱሳን ጋር ቢኖር በእምነት ጸንቶ ኃጢአትን ትቶ ንስሀ ገብቶ የመዳን ተስፋ አለውና ነው።

ቅዱሳን ሕያዋን እንደሆኑ ሲናገር በማቴ 22፥32 "የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አይደለሁም" እንደተባለ እነ አብርሃም፣ ይስሀቅና ያዕቆብ ሙታን ሣይሆኑ ሕያዋን ናቸው። ሕያዋን የተባሉ ቅዱሳን ነፍሳቸው በእግዚአብሔር



እጅ ነውና መዝ 33፥22 ማር 12፥27 ሐዋ 7፥59 1ጴጥ 4፥19 እንዲሁ ጌታችን በሉቃ 24፥5 ላይም ሊፈልጉት ወደ መቃብሩ ለመጡት "ሕያውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ?" በሎዋቸዋል እርሱም አምላካችን "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። ሕያው የሆነ የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለለም አይሞትም። " ዮሐ 11፥25-26

⇒ ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉ፡- ሕያዋን የተባሉ ቅዱሳን ኃጢአት ቢሰሩ፣ ቢበድሉ፣ እግዚአብሔርን በማሳዘን ቢመላለሱ፣ ሕጉን ቢያፈርሱ፣ ቢጥሉ የዘላለም ሞት (ሞተ ነፍስ) እንደሚደርስባቸው ያውቃሉ ማለት ነው። በሕዝ 33፥12 "በበደለበት ቀን የጻድቅ ጽድቁ አያድነውም" ይላል። እንዲሁ ሁሉ ሁለተኛ ሞት የሆነ የነፍስ ሞት እንደሚደርስ ሲያሳይ በራዕ 21፥8 ላይ "ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍሰ ገዳዮችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባህር ነው ይውም ሁለተኛ ሞት ነው።" ብሎናል።

ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉ ማለት ንስሀ ባይገቡ በደላቸውን ተሸክመውት ቢሞቱ ስቃይ መከራ ወዳለበት እንደሚወድቁ እንደሚጣሉ ያውቃሉ ማለት ነው። ዘፍ 3፥17-19 ሕዝ 18፥20 2ኛ ጴጥ 3፥11-13 ያዕ 1፥15 ማር 7፥21

⇒ ሙታን አንዳች አያውቁም፡- ሙታን የተባሉ በሁለት መልኩ ይገለፃሉ። አንደኛው ነፍስ ከሥጋው ከተለየች በሥጋው የሚሆነውን የሚከሰተውን አያውቅምና የሥጋን ፈራሽነት ያስረዳል። ነፍስ የተለየችው ሥጋ አላዋቂነቱን ያስረዳል። ዘፍ 3፥19

ሁለተኛው በሕይወት እያሉ ምግባር ከሃይማኖት ሣይኖራቸው በዚህ ያልዳኑትን ሙታን ይላቸዋል "ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው" ሉቃ 9፥60, ማቴ 8፥22 እነዚህ ሙታን ነፍስ /ሙታነ አእምሮ/ ይባላሉ። ከዚህ ሙታነ አእመሮ የሚነሱ የፊተኛው ትንሣኤ ባለበት ይሆናሉ።

ሁለተኛው ሞት ያልነው በነዚህ ላይ አያሰራም ምክንያቱም በፊተኛው ትንሣኤ ሕይወታቸውን ይለውጣሉና በራዕ 20፥6 "በፊተኛው ትንሣኤ እድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው ሁለተኛው ሞት በነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም" በኃጢአት ተይዞ መኖር መተኛት፣ ማንቀላፋት ነው። ንስሀ መግባት ግን ከኃጢአት እንቅልፍ መንቃት ነውና ሮሜ 13፥11

፩

ሙታን እንዳች አያውቁም ያለው ፣በሥጋቸው የሞቱ ንስሀ ያልገቡ ሙታን እንዲሁ ደግሞ በምድር እየኖሩ ኃይማኖት ከምግባር ያልያዙ ሙታን ምንም አያውቁም መታሰቢአቸው ጠፍቶአልና ነው።

ቅዱሳን ግን ያውቃሉ ሁሉን የረዳሉ።

- 1ኛ ቆሮ 2፥10-12 "...ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም" ቅዱሳንን ከሙታን ጋር ማመሳሰል የእግዚአብሔርን መንፈስ ማቃለል ነውና "መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ኃጢአቱ አይስተሰረይለትም" ሲል ተናግሮአልና።
- 1ኛ ቆሮ 13፥12 "...የዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ አውቃለሁ።" ቅዱሳን እንደ ኃጢአተኞቹ አላዋቂ ሳይሆኑ ያውቃሉ። እነዚህን ጥቅሶች መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመልከት ዘፍ 18፥1-33, ዘፍ 32፥24-30, ዘፀ 3፥1-7, ዘፀ 25፥20-22, ዘፀ 33፥7-11, 1ኛ ነገስ 9፥1-3, 1ኛዜና 11፥18, ኢሳ 6፥1-3, ሐዋ ሥራ 7፥55-56, 2ኛቆ 12፥1-7

⇒ መታሰቢያቸው ተረስቶአል፦ መታሰቢያቸው ተረስቷል የተባሉ ቅዱሳን ሳይሆኑ በምድር ሲኖሩ በጎ ሥራ የሌላቸው በቅድስና ያልኖሩ ኃጥአን



መታሰቢያ የላቸውም ለማለት ነው። ቢታወሱ እንኳ በክፉ ሥራቸው እንጂ በበጎ ሥራቸው አይደለም። እንደ ናቡከደነጸር፣ እንደ ሂትለር ሞሶሎኒ በሌሎችም በመጽሐፍ ቅዱስና በአለም ታሪክ የምናገኛቸው በበደል የኖሩ አንበሶች (ኃያላን) ሆነው የኖሩ ምንም መታሰቢያ የላቸውም ከፉዎች ሆነው ሄደዋልና ለጽድቅ የበቃ አንዳችም ሥራ የላቸውም።

ነገር ግን ቅዱሳን መታሰቢያቸው ለዘላለለም ነው። መዝ 111፥6 "የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል።" ይላል ይረሳል አላለም ጌታ እግዚአብሔርም ለዘላለም የመታሰቢያ ስማቸው እንደማይጠፋ ተናግሮአል። "እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ የመታሰቢያ ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ። "ኢሳ 56፥4-6 እግዚአብሔር በቤቱ በቅድስት ቤ/ክርስቲያን በእኛ በእያንዳንዳችን የማይጠፋ ስም ሰጥቷቸዋል። በሚካኤል፣ በገብርኤል፣ በማርያም፣ በጊዮርጊስ፣ በተክለሃይማኖት፣ ወዘተ ስም የሚታነፁ ቤ/ክርስቲያን የሚመለክበት የሚገለገልበት ክርስቶስ ሲሆን ነገር ግን መታሰቢያነቱ ለቅዱሳን ተሰጥቷአል። ለምን ቢባል የመታሰቢያ የዘላለም ስም እሰጣችኋለሁ ብሉአልና ዳዊትም "ገብረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ ያሰው ለዚሁ ነው። መታሰቢያነቱ ለዘላለም ስለሆነ ጊዜያዊ ስላልሆነ የማይጠፋ

ስም አላቸው ኃጥአን ግን የላቸውም፣ ክፉዎች ግን የላቸውም። ቅዱሳን ስማቸው ብቻ ሳይሆን በጽዋ ውሃ እነሱን ያሰበ ዋጋው አይጠፋበትም ማቴ 10፥41 ይህ ቃል የእግዚአብሔር ነው። እንዳሁ በምሳ 10፥7 "የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው።" ይላል መታሰቢያቸውን ማድረግ በረከት እንዳለው መ/ቅዱስ ያስረዳናል።

ስለዚህ መታሰቢያቸው የተረሳው የኃጥአን እንጂ የቅዱሳን አይደለም፣ ይህ ለቅዱሳን የተነገረ ቢሆን ኖሮ ዳዊት መታሰቢያቸው ለዘላለም ይኖራል

ባላለን፣ ኢሳያስም የዘላለም መታሰቢያ ስም እሰጣቸዋለሁ ብሎ እግዚአብሔር መናገሩን ባልዓፈልን ነበር። ከላይ የተመለከትነው መታሰቢያ ስም እንዳላቸው እንጂ የቅድሳን መታሰቢ የሚረሳ አለመሆኑን ነው። ኃጥአን ግን መታሰቢያ የላቸውም ተረስቷል። ቅዱሳን እንኳን መታሰቢያ ላይኖራቸው ቀረቶ ከማማለድም አልፎ እስከ መፍረድ ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል። ማቴ 19፤28

ይህን ላልተረዱ የልድያን ልብ ከፈቶ ያስረዳ አምላክ ይህን ድንቅ እውነት ያስረዳልን ሐዋ 16፤15-16

## ምዕራፍ አምስት

## ልሳን

በተለይ በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የፕሮቴስታንት የእምነት ቡድኖች እንደ ትልቅ ስጦታ የሚቆጥሩት ልሳንን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ካሉት ስጦታዎች ሁሉ ትንሹና የመጨረሻ ስጦታ እንደሆነ ያነግረናል። ከእውቀት፣ ከእምነት፣ ከመፈወስ፣ ትንቢትን ከመናገር፣ ከነዚህ ሁሉ የመጨረሻው ስጦታ ልሳን ነው። 1ቆሮ 12፤9-11 "እንግዲህ ደግሞ እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ፣ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ" 1ቆሮ 14፤12 ቤተክርስቲያንን የሚያንጸት ደግሞ ትለቁ ስንታ የሆነው ፍቅር እንጂ ልሳን አይደለም። በመጽሐፍ ቅድስ ላይ እንደምንመለከተው ቤ/ክርስቲያን ሊያንጽ የሚችል ከእግዚአብሔርም ክብር የሚያሰጥ ፍቅር እንጂ ልሳን አይደለም።

- "እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሶስቱ ፀንተው የኖራሉ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።" 1ኛ ቆሮ 13፤13
- "በሰዎችና በመላዕክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኸ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሸው ጸናጽል ሆኛለሁ።" 1ቆሮ 13፤1 ለዚህም



ይመስላል ልሳንን ብቻ ሲያስቡ ፍቅርን ስለተው በአሁኑ ሰአት በፕሮቴስታንቶች መካከል የሰይጣን ሥራ የሆነው መለያየት እየበዛ ሲመጣ የምናየው።

- "ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም ትንቢትም ቢሆን ይሻራል ልሳኖችም ቢሆኑ ይቀራሉ" 1ቆሮ 13፤8 ለሚቀር ነገር ያን ያህል ከመድከም ሊወድቅ የማይችለውን ፍቅር መያዝ በበስጠባቸው ነበር። ለተቸገረው አይራሩም፣ እነሱ የሚጠቀሙበት ከሆነና እምነታቸውን ሊቀበል ፈቃደኛ ከሆነ ይረዱታል፣ ካልሆነ ግን ለምስኪኑ እንኳን ራርተው ሊሰጡ የሚሰጡትን እንኳ ያከላክላሉ ጌታ ግን ለሚለምነን ሁሉ እንድንሰጥ አስተምሮናል። ሉቃ 6፤29 ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ፈጸሞ የማያደርሰውን ልሳንን ለማግኘት ሲደክሙ እናያለን ያውም እነሱ ተገለጸለን የሚሉት አውነት እንኳ ቢሆን አንድ ነገር ነው። ግን ልሳኑም በመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይገናኝ ውሸት፣ እንዲሁ ጫጫታና ሁከት እንደገናም ደግሞ በዚህ ላይ ፍቅር ማጣት ተጨምሮበታል። አርቴፊሻል የሆኑ የትህትና ሂደቶች አሉ ግን እውነተኛ ትህትናን አልተላበሱም። ትህትና እኮ ቢኖር ራሳቸውን ከቅዱሳኑ ጋር ለማማወዳደር ባልደፈሩም ነበር ለምስኪኑም በራሩ ነበር።
- "እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር በማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታል። አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፣ በውሸት አትመስክር፣ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትዕዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል። ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።" ሮሜ 13፤8-10 ቤ/ክርስቲያንን ለማነጽ አብዝቶ የሚያስፈልገንን እንዲህ ያለው ፍቅር እንጂ ልሳን አይደለም። ለዚህም ነው ቅ/ጳውሎስ "በልሳኖች ከሚናገር ይልቅ ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል" ያለው 1ቆሮ 14፤5
- "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" 1ኛ ዮሐ 4፤8 እግዚአብሔር የሚከብረው በልሳን ሳሆን በፍቅር ነው የበለጠውን፣ ስጦታ ትተን ላነስ ስጦታ ሰዎችን

ማሯሯጡ ሲያውም ላልተጣራ ልሳን እንዲህ መሆኑ የሚገባ አይደለምና ከልሳን ይልቅ የሚበልጠውን ፍቅርን መፈለጉ ይሻላል።

## 5.1 ስጦታዎች የሚሰጡ እንጂ የሚጠየቁ አይደሉም

እግዚአብሔር የፈለገውን ስጦታ በወደደው ጊዜ ለፈለገው ሰው ይሰጣል ሁሉ ነገር እኛ ስለፈለግነው ወይ ስለጠበቅነው አይሆንም ይልቁንስ ይህን አጋጣሚ ሰይጣን እንዳይጠቀምበት መንገዱን መዝጋት ይገባል። ብዙዎች ፕሮቴስታንቶች (ጴንጤዎች) ለስጦታዎች ሲስገበገቡና እጥብቀው ሲሰሙ ይታያሉ። ስጦታዎች ግን እንዲህ ባለው ነገር አይሰጡም ጌታም ይህን ሲያስረዳ "የእግዚአብሔር መንግስት በመጠባበቅ አትመጣም" ሉቃ 17፡20 ብሎናል።

ስጦታ የሚጠየቅ ሣይሆን የሚሰጥ ስለሆነ ሐዋርያው "እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነት መጠን እንዳካፈለው ይሰጠዋል" ሮሜ 12፡3 በጣም የሚገርመው የልሳን ስጦታ ለሁሉም አይደለም ግን የልሳን ስጦታ አለን የሚሉ ሰዎች ስጦታው የሌላቸውን ሲንቁና ወደ ታች ሲመለከቱ መታየታቸው ነው።

ስስጦታዎቹ የተገባ አለመሆኑን በመረዳት ራስን ዝቅ አድርጎ መመልከት ጥሩ ነው። እነርሱን ለመሸከም የሚያበቃ የልብ ትህትና የለኝም እግዚአብሔር ሲሰጠኝ ከወደደ እኔ ሳልጠይቀው ይሰጠኛል ስለዚህ እኔ ግን ከትዕቢት እንድድን ትህትናን ይሰጠኝ ዘንድ እጠይቃለሁ ብሎ እግዚአብሔርን መለመን ይሻላል ምክንያቱም እራሴን ከምችለው በላይ ለሆነ መንፈሳዊ ፈተና አላጋለጠውም።

እግዚአብሔርን ጥሩ ስጦታ ልትጠይቅ ከወደድክ የተራራውን ስብከት መመልከት በቂ ነው። "ነገር ግን አስቀድማችሁ ጽድቁን ፈልጉ ሌላው ይጨመርላችኋል" ማቴ 6፡34 አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ቀድማችሁ ስጦታዎችን ፈልጉ ይለን ነበር። ጽድቁን ቀድሞ መፈለግ ግን ሌላውን እንደሚያስጨምርልን ይነግረናል።

## 5.2 ልሳን ምንድን ነው ትርጓሜውስ

ስለ ልሳን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በግልጽ ተነግሮአል የመጀመሪያው ልሳን ተቀባዮችና አገልጋዮች ሐዋርያት ናቸው። በሐዋ 2፡1-13 ያልነውን እያንዳንዱን እያየን እንሄዳለን።

- ቁጥር 1-4 ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው ሳሉ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውንና እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች እንደታያቸው ይገልፅልናል።
- ቁጥር 5-6 "ድምፁን የሰሙት ነሰዎች ወደ ሐዋርያት ተሰባሰቡ በዚህን ጊዜ የተሰበሰቡት ሕዝብ በሙሉ በየገዛ ቋንቋቸው ሲናገሩ ሰሟቸው" ይላል። አስተውሉ ልሳን ምንድነው ብለን ለምናነሳው ጥያቄ ልሳን ቋንቋ ነው። በየገዛ ቋንቋቸው ይላልና የተለያዩ አገሮችን ወይም የተለያዩ ሕዝቦችን የተለያየ ቋንቋ መናገር መቻላቸውን ይነግረናል።
- ቁጥር 7-8 "ተገርመው ተደንቀውም እንዲህ አሉ እነሆ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?" ክርስቲያኖች ያ የተሰበሰበ ሕዝብ ከተለያዩ ቦታዎችና ሃገሮች የተሰበሰቡ ነበሩ። ሐዋ 2፡9-11 ግን ይህ የመጣ ሕዝብ በየራሱ ቋንቋ ሲናገሩ ሰማቸው። ይኸውም አይሁዳውያን የነበሩት የገሊላ ሰዎች ቋንቋቸው ዕብራይስጥ ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን የብዙ የተለያዩ ሃገሮችን ቋንቋ ተናገሩ። እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ትልቁ እውነት ያለው። ዛሬ ፕሮቴስታንቶች እንናገራለን የሚሉት ልሳን ፈጽሞ እንደ ሐዋርያት አይደለም አይገናኝም በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰማው የለም።

ሁለተኛ ደግሞ የየትኛው ሀገር ወይ ሕዝብ በቋንቋ ነው? "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጸችኋል" ይለናል። ኤፌ 2፥20 እንግዲህ ሐዋርያት የተናገሩትን ሰምተዋቸዋል። ቋንቋቸው ስለነበር ሕዝቡ አዳምጦአቸዋል፣ ለዚህም ነው የተደነቁት የተገረሙት። ሐዋ 2፥11 ላይ ስንሄድ የተሰበሰበው ሕዝብ ስለተናገሩት ልሳን ምስክር ነበር። "ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን።" በማለት ስለማን እንደተናገሩ በእያንዳንዳቸው ቋንቋ ስለማን እንዳወሩ ግልጽ አድርገውታል። ዛሬ ፕሮቴስታንቶች እንናገራለን የሚሉት ልሳን ተናጋሪውም ሰሚውም የማያውቀው ስድብ ይሁን ርግማን ይሁን ለይቶ የሚመሰክርለት የሌለው ነው።

### 5.2.1 እንዴት አዲስ ቋንቋ ተባለ አሁንስ?

አዲስ ቋንቋ ያሰኘው ሌላ ሳይሆን ቋንቋውን የሚናገረው ሰው በሌሎች አገሮች ቋንቋ ለመናገር የበቃው ተምሮ፣ ወይ ኖሮበት፣ ወይ በቤተሰብ አግኝቶት፣ ወይ ቋንቋውን ሊናገር እንዲችል ሊያደርገው የሚያዘቃ አንዳች ነገር ሳይኖር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተለያዩ ቋንቋዎች መናገር እንዳችል ያደርገዋል። ስለዚህም ከሚያውቀው ቋንቋ ውጪ የሌሎች ህዝቦች አገሮችን ቋንቋ መናገር በመቻሉ አዲስ ቋንቋ አለው እንጂ ሌላ አይደለም።

ለምሳሌ አማርኛ ቋንቋ በመኖር በመወለድም የአገሪቱም ብሔራዊ ቋንቋ ስለሆነ በልምድ ይናገራል፣ እንግሊዝኛን ደግሞ በትምህርት ወይ በአካባቢው ስለሚነገር ሊናገር ይችላል። እነዚህን ሁለቱን ቋንቋዎች የሚናገረው ሰው ፈረንሣይኛ፣ አርመንኛ፣ አረብኛ፣ ጀርመንኛ፣ ኦሮምኛ፣ ትግርኛ አይችልም፣ አያውቅም። እግዚአብሔር ይህን ሰው እንዲያገለግል ስለፈለገው እነዚህ የማይችላቸውንና የማያውቃቸውን ቋንቋ ይገልጽልታል



ያን ጊዜ ሰውየው በሌሎች ልሳኖች በተናገረ በአዲስ ቋንቋ ተናገረ ይባላል። የልሳን ትርጉሙ ይህ ነው።

እንግዲህ ይህን እውነት ይዘን ስንሄድ ሐዋርያት የተናገሩት ልሳን የሚሰማ ስለማን እንደተናገሩ የሚታወቅ ነበር። ምንያቱም ሰው ራሱ መስክሮአልና ሐዋ 2፥9-12

ነገር ግን ይህ ጉዳይ ተነስቶ ለፕሮቴስታንቶቹ መልስ በሚለጣቸው ሰአት "ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተዋል" ያሏቸው ስላልሰሙት ነው ለማለት ይቃጣቸዋል። ሐዋ 2፥13 ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተዋል ያሏቸው ስላልሰሟቸው ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር የሚያወሩላቸው ፈጽሞ ሊገባቸው ስላልቻለ ነበር። መስማታቸውንማ ነግሮናል። ግን የሚነግሩዋቸው ቃል ከሚያውቁትና በፍልስፍናቸው ከተማሩት በጣም አዲስና እንግዳ ትምህርት ስለሆነባቸው ጉሽ ወይን ጠጅ ጠጥተዋል አሉ እንጂ ስላልሰሙት አይደለም። ቅዱስ ጴጥሮስም ይህ እንዳልሆነና እግዚአብሔር በትንቢቱ የተናገረውን እየፈጸመ እንደሆነ ገልጾላቸዋል። ሌላው የሚያነሱር ጥቅስ 1ቆሮ14 ላይ ያለውን ነው።

እኛ የምንናገረው የማይሰማው 1ኛቆሮ 14፥2 "የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም የሚያስተውለው የለምና" ይላል ይላሉ። አዎ ቃሉማ ይላል ቃሉ ግን ያለው የሚሰማው የለም ሳይሆን የሚያስተውለው የለም ነው። ይህም የሚገባው፣ የሚረዳው የለም እስ እንጂ ቋንቋው ምን የማን እንደሆነ የሚሰማው የለም አላለም። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ "ዋሽንትም፣ ክራርም ድምፅ ሲሰጥ የድምጽን ምልክት ካለየሁት ምን ይጠቅመናል። ለንፋስ የምትናገሩ ትሆናላሁ" ያለው። 1ቆሮ 14፥7-9 ስለዚ ልሳናት አንዳችም ምንም የሚጠቅሙት ነገር የለም።

"በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል።" ይህ ማለት የሚገልጠው መልካም የሆነውን ቃል ነው ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብና ድኅነት ያለበት ቃል ነው እስ እንጂ የማይሰማ ተናጋሪው የማያውቀው አድማጩ የማይሰማው ቃል ይናገራል አላለም። ቋንቋው ይታወቃል። ነገር ግን በቋንቋው ምሥጢርን ይገልጣል ይህም በመንፈስ ያለ የተገኘ እንጂ ከሥጋ የሆነ ጥበብ እውቀት ያለመሆኑን የሚገልጽ ነው። ታዲያ ዛሬ እነሱ ከሚሉትና ከሚያደርጉት ፍጹም የማይገናኝና የታራራቀ ነው። የአሁኖቹ ፍጹም ውሸትና የአጋንንት መንፈስ ራሱን ለውጦ የገባበት ነው። የሐዋርያት ግን ፍጹም በእግዚአብሔርም በሰው የተመሰከረለት ነው።

"እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ" ያለው ማስታወስ ይገባል። 1ቆሮ 14፥9 ልሳን ለማያምኑት ምልክት ነው እንጂ ለኛ ለምናምን አይደለም። 1ቆሮ 14፥22 ልሳን ያነሰ ስጦታ የመሆኑን ያህል የሚጠቅም አይደለም። እንደውም ስለዚሁ ሲያብራራ "በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው" ይላል። 1ቆሮ 14፥14 አእምሮ ያለፍሬ ሆኖ በምትናገረው ልሳን ፍሬ እንደሌለው ዋጋ እንደሌለው አስቀምጦአል። ስለዚህም ነው "አንተ በመንፈስ ብትባርክ ባልተማሩት ስፍራ የተቀመጠው የምትለውን ካላወቀ ለምስጋናህ እንዴት አሜን ይላል።" 1ቆሮ፥16 ስለዚህም ዝም ቢል የሚመረጥ መሆኑን አስቀምጦታል። 1ቆሮ 14፥28 እንግዲህ ከነዚህ ሁሉ አንፃር ልሳን አዲስ ቋንቋ ከተባለበት እውነታ ጋር በአሁኑ ጊዜ ጠቀሜታ የሌለው ነው።

ሌላው ተርጓሚ ያስፈልጋል የሚለው ገለፃ ተርጓሚ ያስፈለገው ቋንቋውን ስላልሰሙት ሳይሆን በዚያው ቋንቋ የሰሙትን ቃል አብራርቶ የሚገልፅላቸው ማለት ነው። ሁል ጊዜ ተረጓሚ ያስፈልገዋል ማለት አይደለም። መተርጎም የሚገባው ክፍልን ተንትኖ ሌላው እንዲናገር ነው።



ይህን ሁሉ ግን ለማቃለል ጳውሎስ "ልሳንን ከሚናገር ትንቢት መናገር ይበልጣል ማህበሩ ይታነጽ ዘንድ" ሲል ገልጾታል። 1ቆሮ 14፥6

## 5.3 አሁን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አላቸው ወይ?

"መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ" 1ዮሐ 4፥1 መንፈስን ሁሉ ማመን የተገባ አይደለም። ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ አስመስሎ መምጣት ይችላልና። 2ቆሮ 11፥15 ስለዚህ መናፍስትን መለየት ያስፈልጋል።

በእኛ ዘንድ ግን አሁን በፕሮቴስታንቶቹ በኩል የምናያቸው ነገሮች ከእግዚአብሔር መንፈስ እንዳልሆነ ያረጋግጡልናል። መንፈስ ቅዱስ የተሞላችው ኤልሳቤጥ ድንግል ማርያምን አመስግናታለች አክብራታለች ዕንስ እንኳ ስግዲል ሉቃ 1፥39 ነገር ግን ዛሬ መንፈስ ተሞልተናል ሲሉ የምንሰማቸው ለምን ቅዱሳንን ድንግልን መናቅ ውስጥ አስገባቸው ስንል የተሞሉት ከእግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ እነዚህን የቅዱሳንን ክብር መጠበቅ የእግዚአብሔርንም የሆኑትን ከመናቅ የተቆጠቡ ይሆኑ ነበር። ቅዱሳንን የሚቃወም መንፈስ ከአጋንንት ነው። ራዕ 12፥1-17

ቅድስ ጳውሎስ ሲመክረን "መንፈስን አታጥፉ ትንቢትን አትናቁ ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ" 1ኛ ተሰ 5፥19 በዚህ እውነት መሠረት የእግዚአብሔር መንፈስን ሥራ አለማጥፋት የተገባ ነው የሚበልጠውን ትንቢትን ንቆ ወደ ልሳን መሮጥ ጥሩ አይደለም። ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር መጣላት ነው። ሁሉን ፈትኑ እንደተባለ ሰይጣን ባፈረበት በቅዱስ መስቀሉ የእግዚአብሔርንና የሰይጣንን መንፈስ መለየት እንችላለን። ስለዚህ የመስቀሉ ኃይል ያስፈልገናል። 1ቆሮ 1፥18

እንግዲህ እኛ ከምንወስደው አጠቃላይ ሃሳብ በአብዛኛው በፕሮቴስታንቶች ዘንድ መንፈስን ሁሉ የማመን ነገር ስላለ አጋንንት የብርሃን ሥራ አስመስሉ የሚሰራባቸው ወቅቶች በዝተው ይታያሉና መንፈሱን መርምሩ እንላቸዋለን።

የኢየሱስን ስም እየጠራን እንዴት? ይባል ይሆናል አጋንንት እንደሚያምን መዘንጋት የለበትም ያዕ 2፤19 ለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ "ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ አይድንም" ያሰው። ማቴ 7፤20-23 ለመዳን ደግሞ ወሳኙ ኢየሱስ ኢየሱስ ማለት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ነው። ፈቃዱ እርሱንና የእርሱ የሆኑትን አውቀን በፍቅር መመላለሳችን ነው።

ስለ ልሳን በፈረንሣይኛ ቋንቋ የቀረበውን መረጃ መጨረሻ ገጽ ላይ ይመልከቱ።

እግዚአብሔር ማስተዋሉን ይስጠን

ይቆየን



# REFERENCE

Intercession-n of action

(Sense it does not occur in ancient L it is found in F from 15th c.) The action of interceding or pleadingon behalf of (rarely against) another: entreaty solicitation; or prayer for another;' mediation.

1534 TINDALE Rom. Xi2 what the scripture sayth by the mouth of Heilas how he maketh intercession to God agaynst ISREL 1548 Hall chron, VIII 1416. I will send to the kyng and make humble intercession for your pardon. 1588 DROGERS in Ellis orig. Letf. Ser. II III 145 Certaine goods... conficated the day before I came, were by my quicke intercession all released. 1659 Willford I will here interpose a few lines betwixt them and the copy as an intercession for the printer who is less culapble.

b. spe. in religious use

1726 LAW Serious C.XXI, intercession in a great and necessary part of Christian Devotion. 1782 PRIESTLEY corrupt, Chr 1,IV 377 Justinian (made) use of he intercession of the virgin.

1848 R.I WILBERFORCE we are to address God only through him whose intercession as man is the ground of our hope.

les trois idiomes sont celui des Juifs, celui des Grecs et celui des Latins parce qu'ils figuraient seuls sur l'écriteau de la croix.

Idiolecte: -utilisation personnelle d'une langue par une seule personne.



## የፈረንሣይኛ ቋንቋ መረጃ ትርጉም

ስለ ማግለድ

ከለ ሮበርት በፖልሮበርት መዝገበ ቃላት መሠረት 1984 እትም በ1223 ዓ.ም. ስለ ማግለድ ሁኔታ ኢንተርሴሽን አማላጅነት ጣልቃ መግባት ማስታረቅ ሲል ይፈታዋል

በዚህ አመት ማለት በ1223 ዓ.ም. ድንግል ማርያም አማላጅ ናት ሲል ይገልፀዋል ኢንተርሴዴ በ1345 ኢንተረሴዴር ከሚል የላቲን ቃል የመጣ ነው።

- በነ ሰው የምታደርገው በጎ ነገር
- መለመን የአንድ ሰው ጠበቃ መሆን በጥሩ ሁኔታ ማለት በቀላሉ ያደደለ ሰሌላው የሚደረግ ልዩ የሆነ ልመና
- መከላከል ለምሳሌ ያሀል ከአለቃው ጋር ላለ ጉደይ ስለ አንዱ ሰው መናገር መወከል ምክንያቱም በኋለኛው አዳም የተከናወነልን የአዳምን ጥፋት የመደምሰስ ሂደት
- መጠበቅ ከሆነ ነገር ማለት በፈረንሣይኛው አገላለጽ ጉዳት ሊያደርስ ከሚችል ነገር ሲል ይገልፀዋል ይኸውም Proteger

⇒ ኢንተርሴሰር አማላጅ 12/12 ዓ.ም. ከላቲን ነው የመጣው ሃይማኖታዊና ሊተሪያን ቋንቋ ነው

የሚያማልድ ማለት ሲሆን ፕሮተስታንቶች የሚቃወሙአቸው አማላጆች በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የሚለምኑ የሚያገናኙ።

ከኢሚል ሊትሬ የተወሰደ 1964 ዓ.ም. እትም

- የአማላጅነት ሁኔታ በተጠቀሰበት ቦታ ላይ የመላዕክትን አማላጅነት ከክርስቶስ ጋር የመላዕክቱን ጣልቃ ገብነታቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያልገባቸው በማመሳሰላቸው መሳሳታቸውን ይገልፃል

- በእመቤታችን አማላጅነት የመንፈስ ቅዱስን በረከት ወዲያው ለማግኘት እንለምን

ስለ መማለድ

- ስለአንድ ሰው ብለህ ጣልቃ መግባት
- ኢንተር መሀከል ሴዴ መሄድ ኢንተርሴዴ በመሀከል መሄድ

ስለአማላጅ

- የሚያማልድ
- መላዕክት ከእግዚአብሔር ዘንድ አማላጆቻችን ሆነው ሳለ እኛ ግን በየቀኑ ብዙ እናሳዝናለን።
- ይህ ቃል በድሮ ጊዜ የተሰጠው የአንድ ኤጴስ ቆጶስ ቦታ ክፍት ሲሆን ለአንዱ ቄስ እንዲያስተዳድር የሚሰጥ ቦታ በማለት ይገልፀዋል።

ጠቅለል ባለ አመለካከት ስለ ድንግል ማርያም

ሞገስ የሚለው ጸጋ የሚለው "ግራቲያ" ከሚል የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን የእግዚአብሔር ርዳታ ማለት ነው። በሃይማኖት ከተፈጥሮ በላይ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸምበት ወደ እግዚአብሔር የምንደርስበት ልዩ የሆነ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ርዳታ

- ከአንድ ሰው ጥሩ ጎኑን ደግ ጎኑን ማግኘት መቻል
- ሞገስን እግዚአብሔር የሚሰጠው በተለያየ ነገር ላይ ነው።

ተመሳሳዩ- ደግነት፣ ጥበቃ፣ ተወዳጅነት፣ ክብር፣ ምርቃት፣ መንፈሳዊ ክበር



## Add Reference for Good News Bible (GNB)

- Intercede (vi) - plead (with sb for or on behulf of sb. else) intercession.
- Intercend in-ter-sed v.i. To act peacemufrer between two, to plead (for one) - intervedent (adj.) n. interceder (L.interceder-cessum- inter between, cedire to go)
- Pleading- imploring -n, to act of putling forward or conduction a plea: (in pl) the statements of the two parties in alawsuit;
- special pleading -unfair or one sided argument aiming rather at viatory than at truth. (O.fr plaidier)
- Plead-to offer in excuse

Source- CHAMBNERS ENGLISH Dictionary -265,000 Definitions 190,000 Referenes.

- Plead V.legal of a lawyer (GNB) ings- replies to accusations
- Plead N.excuse Vi. Maker earnest appeal, address court of law, US, pleading
- Advocate (KJB) one who pleads the couse of another; esp. court of law
- person who speaks in favour of sb. or sth.
- Plea defendant's answer to acharge in a law court, appeal, excuse
- Source: Oxford - Advance learner's dictionary
  - Collins Gem Dictionary
  - Mini referenee dictionary
  - Master English Dictionary

## ዋቢ መጻሕፍት


1. የእንግሊዝኛ የተለያዩ እትሞች
   KJB, GNB, NEB, KV, AB, ...
2. የፈረንሣይኛ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ
3. Theology Books 964
4. Dictionary of The Bible 1909
5. Calendar Books 1933
6. Emile Littré 1964
7. Le petit robert par A. Rey et j. Rey-Debove 1984
8. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አማርኛ መዝገበ ቃላት
9. የ Oxford University ጥንታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መዝገበ ቃላቶች
10. አንፃራዊ ትምህርተ መለኮት
11. ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ
12. አምደ ሃይማኖት
13. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን እምነት ሥርዓት አምልኮትና የውጭ ግንኙነት
14. የቅዳሴን አማላጅነት
15. ከኩሐ ሃይማኖት
16. ሃይማኖተ አበው
17. የግዕዝና የአማርኛ አዲስ ኪዳን
18. The prophecies of Daniel and Revelation - 1944
19. በቤተክርስቲያናችን የሚወጡ መጽሔቶችና ጋዜጦች





ዲያቆን አሐዱ አስረስ
☎ 20 28 17
09- 61 86 15
✉ 182320
Email-ahadu_aseres.2003@yahoo.com.
አስተያየት ሃሳብና ጥቆማ ላላችሁ